# ብዕረኛው!

ከዓሣዬ

04/22/2010

የፋሺስት ባለሟል የኢሰፓው ኣውራ
ንስሃን የማያውቅ ሃይሉ ኣርአያ፣
እሱ ብሎ ምሁር የታሪክ ሥላቂ
ዛሬም እንደ ትላንት፣
ታጋዩን ኮንኖ ገዳዩን ኣድናቂ
በደም የጨቀዬ ታሪኩን ናፋቂ ።

ታድያ፣
እኔ ምን ቸገረኝ ብዕረኞች ካሉልኝ
እያወራረዱ ሃይሉን ሲያቅሙልኝ
የሣልቫጅ ምሁራንን ጣቱን ሲቆምጡልኝ
ፊልም ቀራጭ ባንዳውን ሲያኮማትሩልኝ
መቸሥ ምን እላለሁ፣
ብዕራችሁን ይባርከው፣እናንተን ያኑርልኝ! ።

የባንዳ ዲቃላን ኣረሞ ነቅላችሁ
የታሪክ በራዡን ባፍ ጢሙ ደፍታችሁ፣
ላንድ ኣፍታ እንኳን ቢሆን ፋታ ሣትሰጡት
ዳግም ላይነሣ እንጦርጦሥ ሥደዱት ።

ያባታችሁን ጋሻ ጦራችሁን ሰብቃችሁ
ፋሺስት ዘረኛውን ከትቢያ ቀላቅላችሁ
በኢትዮጵያዊው ቀለም በብዕራችሁ ደምቃችሁ
ዛሬም እንደ ጥንቱ እንደ ሰማዕቶቹ
ለሃገር ዘብ ቁሙ!
በዓላማ ቁማችሁ፣በቃልኪዳን ጸንታችሁ! ።

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.